# ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች - የልዩ ፍላጎት ትምህርት የማገገሚያ አገልግሎቶች የቤተሰብ መመሪያ

**የማገገሚያ አገልግሎቶች ምንድናቸው?**ይህ ቃል OSPI በወረርሽኝ ምክንያት በ IEP ግቦች ላይ ተገቢው መሻሻል ያላሳዩ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ተጨማሪ የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ለመግለፅ ይጠቀምበታል።የማገገሚያ አገልግሎቶች ከየማካካሻ ትምህርት እና የተራዘመ የትምህርት ዓመት አገልግሎቶች የተለዩ ናቸው፡፡የማገገሚያ አገልግሎቶች ከቅድመ መደበኛ ትምህርት እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ IEP ያላቸው ተማሪዎች ሊሰጡ ይችላሉ፣ነገር ግን ሁሉም IEP ያላቸው ተማሪዎች የማገገሚያ አገልግሎቶች ያስፈልጋቸዋል ማለት ኣይደለም።

**ልጄ የማገገሚያ አገልግሎቶችን እንዴት ያገኛል?** ኬዝ ማናጀሮች ስለ የማገገሚያ አገልግሎቶች እና እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት የሚደረገውን ሂደት ጨምሮ እነዚያ አገልግሎቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ መረጃ ለመስጠት ከቤተሰቦች ጋር ይገናኛሉ።የሚያስፈልጉትን የማገገሚያ አገልግሎቶች የመወሰን እና የማቀድ ውይይቶች በዚህ የፀደይ ወቅት፣መኸር ወቅት ወይም በ2021-2022 የትምህርት ዓመት ውስጥ ሊካሄዱ ይችላሉ።ውሳኔዎች፣ዲስትሪክቱ እና ወላጅ ከተስማሙ የ 2021–22 የትምህርት ዓመት ከመጀመሩ በፊት፣ከዓመታዊው የIEP ስብሰባ በፊት ወይም ወይም በመጪው ዓመታዊ የግምገማ ቀን ላይ ሊካሄድ ይችላል።




**የማገገሚያ አገልግሎቶች ምን ይመስላሉ?**

- የማገገሚያ አገልግሎቶች በየድስትሪክቱ የትምህርት ቀን /ዓመት ውጭ ወይም በትምህርት ቀን ውስጥ ሊሰጡ ይችላሉ።
- የማገገሚያ አገልግሎቶቹ ምን ያህል፣ምን ዓይነት እና ምን ያህል ጊዜ እንደሚሰጡ በእያንዳንዱ የተማሪ ፍላጎት ላይ በመመስረት ይወሰናል።
- የማገገሚያ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ:ተጨማሪ የበአካል ትምህርት፣የበአካል ወይም የቴሌቴራፒ አገልግሎቶች፣ተጨማሪ የሽግግር አገልግሎቶች፣ተጨማሪ የርቀት አገልግሎቶች፣ከትምህርት በፊት ወይም በኋላ ወይም በዕረፍት ጊዜ፣ቀድመው በሚለቀቁበት ቀናት የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፣ተጨማሪ የበአካል የተዋቀሩ የጨዋታ ቡድኖች ወይም ከትምህርት በፊት ወይም በኋላ ወይም በዕረፍት ጊዜ የእኩዮች ማህበራዊ ቡድኖች።

**ጥያቄዎች ካሉኝስ?**

- የተማሪዎ ኬዝ ማናጀር ወይም አስተማሪ ያነጋገሩ።
- የOSPI የማገገሚያ አገልግሎቶች መመሪያ ይከልሱ: https://www.k12.wa.us/sites/default/files/public/specialed/pubdocs/WA-Roadmap-SpEd-Recovery-Services-2021.pdf።
- የልዩ ፍላጎት ትምህርት ዲፓርትመንት በspecialed@seattleschools.org. ያነጋግሩ።